# የድሬዳዋ አስተዳደር

# ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ

# DIRE NEGARIT GAZETA

# OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፪

ድሬዳዋ ጥር ፳፮ ቀን ፳፻፲፰ ዓ.ም

በድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Fifth Year No. 92

DIRE DAWA February, 03/2026


## <u>አዋጅ ቁጥር ፺፪/፳፻፲፰</u>

ከኃላፊነት የተነሱ የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳፰/፳፻፲፪ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት መሪዎች፤ ከፍተኛ ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላት፤ የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችና ዳኞች የሚያገኟዋቸውን መብቶችና ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፱ ንኡስ አንቀጽ ፪ (መ) መሰረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## <u>Proclamation No. 92/2026</u>

A Proclamation to Provide for the Rights and Benefits of Outgoing High Government Leaders, Officials, Members of the Council, court president and Judges of Dire Dawa Administration to amend proclamation 28/2012

WHEREAS, it is necessary to provide for the Rights and Benefits of Outgoing High Government Leaders, Officials, Members of the Council, court president and Judges of the Dire Dawa Administration; to amend the proclamation

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 9 (2) (d) of the Dire Dawa Administration Charter Proclamation No 416/2004, the Dire Dawa Adminstration Council it is here by proclaimed as follows,

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የድሬዳዋ አስተዳደር ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፶፱/፳፻፲ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፺፪/፳፻፲፰ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

በአዋጅ ቁጥር ፳፰/፳፻፲፪ ላይ የተቀመጠው ትርጓሜ ለዚህ አዋጅም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫. **ማሻሻያ**

ከኃላፊነት የተነሱ የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት መሪዎች፤ከፍተኛ ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላት፤ የፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፶፱/፳፻፲ እንደሚከተለው ተሻሽሏል

፩. የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንኡስ አንቀፅ ፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ ፬ ተተክቷል ፡፡

"፬". "የአስተዳደሩ ከፍተኛ ሀላፊ" ማለት የቢሮ ሀላፊ ወይም በቢሮ ሀላፊ ደረጃ የተሾመ ሀላፊ ወይም አማካሪ፣ ወይም ምክትል የቢሮ ኃላፊ ወይም በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የተሾመ ኃላፊ ወይም የጽ/ቤት ኃላፊ ወይም በዚያ ደረጃ የተሾመ ሀላፊ ነው፤

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀፅ ፲፪ የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ ፲፫ ተጨምሮበታል፡፡
፲፫ "ምክር ቤት አባል" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት አባል ነው፡፡

፫. የአዋጁ አንቀፅ ፲፮ የሚከተሉት ሁለት ንዑስ አንቀፆች ተጨምረውበት አንቀፅ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና ፪ ሆኖ ተሻሽሏል ፡፡

**"አንቀፅ ፲፮"**

"፩" «በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ከኃላፊነት ለተነሱ የአስተዳደሩ የስራ ኃላፊዎች የተደነገገው የስራ ስንብት ክፍያ የአስተዳደሩ ምክር ቤት፤ አፈ-ጉባኤ፤ ምክትል አፈ-ጉባኤ፤ ጸሐፊና የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሆኖ

1. **Short Title**

This proclamation may be Citied as the "The Rights and Benefits of Outgoing High Government Leaders, Officials, Members of the Council and Judges of Dire Dawa Adminstration proclamation No. 92/2026"

2. **Definition**

The definition indicated in proclamation No. 28/2012 shall be applicable to this proclamation.

3. **Amendment**

Proclamation No. 59/2018 to provide for the Rights and Benefits of Outgoing High Government Leaders, Officials, Members of the Council and Judges of Dire Dawa Administration is amended as follows.

1. Article 2 sub-articles 4 of the proclamation shall be repealed and replaced by the following sub article 4.
"4". "Higher official" means bureau head, or an official appointed as a bureau head, or an advisor appointed as bureau head, or deputy bureau head or an official appointed as a deputy bureau head, or head of an office or an official appointed as an office head or in similar status.

2. In addition to Article 2 sub-Article 12 of the proclamation,

"13'' "Member of the Council'' means member of the council of the DireDawa Administration.

3. Article 16 of the proclamation shall be amended having the following two sub provisions.

**Article 16**

1.The provisions of Article 7 of the proclamation providing for severance pay to an out going executives shall be applicable to an out going Speaker, Deputy Speaker, Secretary, or chairperson of standing committee of the Council and,

ሀ. ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎት የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባል ወይም

ለ. ከአንድ ምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎት በህመም፤ በአካል ጉዳት፤ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከአባልነት የተነሳ አባል የመልካም ስራ አፈጻጸም የስንብት አባል ይከፈለዋል፡፡

“፪” በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሰረት የሚከፈለው የመልካም ስራ አፈጻጸም የስንብትን ክፍያ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎት ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ) ፤ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ጭማሪ ምርጫ ዘመን አገልግሎት ብር 20,000.00 (ሃያ ሺ) እየታከለ ይከፈለዋል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ጥር ፳፮ ቀን ፳፻፲፰ ዓ.ም**

**ከድር ጁሀር**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

a. After serving for not less than one election term, or.

b. due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least half of one election term, severance pay to be paid

2. The amount of severance pay to be paid pursuant to sub-article (1) of this article shall be 50,000.00 birr. 20,000.00 birr shall be added as severance pay for every additional election.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta

**Done at Dire Dawa, on this 3rd day of February, 2026**

**Kedir Juhar**

**Mayor of the Dire Dawa Administration**